# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
ጥብቅና ቆሞ የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 26 ቀን 24/9/67

## የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያሸንፋል::

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በወታደራዊው መንግስትና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የነበረው ቅራኔ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ ነበር::ወታደራዊው መንግስት ህብረተሰባዊነትን በማወጁ:የመሬትን ይዞታ በማስተካከሉ:አንዳንድ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን የሕዝብ በማድረጉ:በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ በመዝመቱ:እነዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዋና ጠላቶች በመሆናቸው:የመንግስቱና የሕዝቡ ትግል ከልዩነቱ ይልቅ አንድነቱ ያመዝን ነበር::ዛሬ ግን ባንድ በኩል በነዚህ ጥንድ ጠላቶች ላይ የሚደረገው ዘመቻ እየተበረዘ ሲሄድ በሌላ በኩል በሰፊው ሕዝብና ለርሱም በቆሙት ተራማጆች ላይ የሚደረገው ዘመቻ እያየለ ሄደአል::ስለዚህም በሰፊው ሕዝብና በወታደራዊው መንግስት መካከል የነበረው ልዩነት በፈጣን እርምጃ ወደአንደኛ ደረጃ ቅራኔ በመለወጥ ላይ ነው::

በደርጉ ውስጥ ያሉ ተራማጆች ነቁበትም አልነቁበትም:ጠቅላላው የጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት አሰራር ወደአድሃሪነት እያዘነበለ ለመሄዱ በፍፁም የማያጠራጥሩ ምልክቶች አሉ::

1ኛ/ ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን:የሰፊው ሕዝብና የደርጉም ተራማጅ ክንፍ ዋና ጠላቶች ያሜሪካን ኡምፔሪያሊዝምና በርሱም አማካኝነት የሚቀነባበሩት የውስጥና የውጭ አድሃሪያን መሆናቸው ለማንም ሰው ግልጽ በሆነበት ወቅት:በነዚህ ፀረሕዝብ ሃይሎች ላይ የማያወላውልና ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ ፈንታ ወታደራዊው መንግስት ተራማጆችን ማሳደድ ይዞአል::ከነገድ ምክር ቤት ወረቀት አባዛችሁ ተብለው ከተያዙት ወደሃያ ከሚጠጉት ሰዎች ውስጥ ሶስቱ አሁንም በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ ናቸው::ከጭላሉ የርሻ ልማት ድርጅት በርከት ያሉ ተራማጆች ተይዘው መታሰራቸው ይታወቃል::በተረፈም ለሕዝቡ ጥቅም መቆማቸው ፈጽመ የማያጠራጥር አንዳንድ ዘማቾች:የወረዳ አስተዳዳሪዎች:የመሬት ይዞታ ወኪሎች ካሉበት ስራ ተባርረዋል፤ ብዙም ታስረዋል::ወታደራዊው መንግስት ከዚህ በፊት ያለአንዳች ምክንያት ያሰራቸውን ተራማጆች አልፈታም::እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ መንግስቱ መላውን የኢትዮጵያን ተራማጆች አሳድዶ ለመያዝና ለማሰር መነሳቱን የሚያመለክቱ ናቸው ብለን እንገምታለን::

2ኛ/ በጠቅላላው ዘማች ሲባል ቀደም በትምህርት ቤትም ሆነ ዛሬ በየገጠሩ ለሰፊው ሕዝብ የቆመ:ማንኛውንም መስዋእትነት ከመቀበል ያልተቆጠበና የማይቆጠብ:በሙሉ ልቡ ከጭቁኑ ሕዝብ ጐን የተሰለፈ መሆኑ እየታወቀ:በዘማችና በባለርስቶች:እንዲሁም የባለርስትን ጥቅም ለመጠበቅ በቆሙ ፖሊሶችና አስተዳዳሪዎች መካከል ግጭት በተነሳ ቁጥር መንግስቱ የአድሃሪዎችን ወገን ሲመርጥ ይታያል::ሰፊው ገበሬና ዘማቹ:እንደዚሁም አንዳንድ ተራማጅ አዝማቾችና ያገር አስተዳዳሪዎች ተባብረው የባለርስቱን መሳሪያ ሲቀሙትና በሕዝብ ላይ ፋሽስታዊ አመጽ እንዳይፈጽም ለፖሊስ ሲያስረክቡት ፖሊስ የባለርስቱን መሳሪያ እየመለሰ ይፈታዋል::ባንዳንድ ቦታዎችም ፖሊስና ባላባቶች ባንድ ወገን ሁነው ሰፊውን ገበሬ ፈጅተዋል::በዚህ አይነት ሁኔታ ወታደራዊው መንግስት ከጨቋኙ ወገን ጋር ደጋግሞ ተሰልፎአል::ባለርስቱ መሳሪያውን መቀማትና መታሰር ሲገባው ዘማቾች እንዲታሰሩ:ወይንም ከየጣቢያቸው እንዲባረሩ ተደርጓል::በርከት ያሉ ጣቢያዎች ተዘግተዋል::

3ኛ/ በየገጠሩ:በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውና በክፍለአገር አስተዳዳሪዎች ስብሰባ ላይ ጉዳዩ የተነሳው 'ነጭ ለባሽ' የተባለው ድርጅት የፊውዳሉ ሰርአቱ የስልጣን ሰንሰለት መሆኑ እየታወቀ:ወታደራዊው መንግስት ባንድ በኩል ገበሬው ለነዚህ ነጭለባሾች እንዲያርስ ለማድረግና በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ነጭለባሾች በሌሉባቸው የደቡብ ክፍለሃገሮች እንዲቋቋሙ ለማድረግ ሞክሮአል::ይህም አዲስ አይነት ባለርስቶችን ለመፍጠር የታቀደ መሆኑ አይካድም::ከደርጉ በመጋቢት 8 ቀን በታዘዘው መሰረት በአድሃሪው በመሃረነ ምንዳ የአስተዳደር ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ በመጋቢት 15

ለየወረዳዎች የተሻረ አንድ ደብዳቤ /ዜሪ/ እንደሚያስረዳው የየካቲቱን የመሬት ይዞታ አዋጅ ለማክሸፍ ኮሚቴ እየተባለ የገበሬዎች ማህበሮችን ሥልጣን የሚቀማ አድሃሪ ድርጅት እንዲቋቋም ከመንግስት ስራ በጡረታ የወጡ ከበርቴዎችና ነጭለባሾች አሁንም ባለርስት ሁነው እንዲቀሩ ለማድረግ በደርጉና በቢሮክራሲው ውስጥ ተንሰራርተው የተቀመጡ አድሃሪዎች ትልቅ ጥረት እንደሚያደርጉ ያስረዳል፡፡ይህ ዜሪ በቀጥታ የመሬት ይዞታ አዋጁን የሚያፈልስ ስለሆነ በየቦታው የሚገኙ ተራማጅ የመሬት ይዞታ ወኪሎችና አስተዳዳሪዎች ከስራ ላይ እንዳይውሉ አድርገውታል፡፡ይሁንናም የተባለው ዜሪ በወጣ ሰሞን መላውን ገጠር ያዳረሰ ቢሆን እርሱን በመሰረዝ የወጣው ትእዛዝ ግን እስከዛሬ በብዙ ቦታዎች አልደረሰም፡፡ይህም አድሃሪዎች ከላይ እስከታች በሚገባ በቢሮክራሲው ውስጥ የተደራጁና የኢትዮጵያን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ በይፋ የሚፍጨረጨሩ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ባሁኑ ወቅት ከመሸፈትም ይልቅ ይህኛው መንገድ የሚያመቻቸው መሆኑን አውቀዋል፡፡መንግስት በነዚህ ላይ አንዳችም እርምጃ አልወሰደም፡፡

4ኛ/ ባለፉት ሁለት ሶስት ወራት በየቦታው፡በየመስሪያ ቤቱ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ባይሆን በፊውዳል ስርአት መሰረት፡በትውውቅ፡በምልጃ፡በሴራ ወዘተ. የተሾሙት ግለሰቦች ሕዝብ ያወገዛቸው አድሃሪዎች መሆናቸው እየታወቀ፡ባሁኑም ቦታ ሳቦታዥ ለማድረግና እንቅስቃሴውን ለመቀልበስ ምንም ከማድረግ እንደማይቆጠቡ በተግባር እያሳዩ፡እነዚህ ግለሰቦች በቦታቸው እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ከነዚህ ሰዎች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡— ያገር አስተዳደሩ መሀረነ መንግ፡የርሻ ሚኒስትሩ፡የህዝባዊ ኑሮ እድገት ተፈራ ሃይለስላሴ፡የጉዳሙ አስተዳዳሪ፡የቀደሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የአክሊሉ ቀኝ እጅ የነበረው አክሊሉ ሀብቴ የታወቁ አድሃሪዎች ናቸው፡፡

5ኛ/ ወታደራዊው መንግስት ተራማጆችን እየለቀመ ይሰር እንጂ እነደጃዝማች ብርሃነ መስቀል፡መርእድና መስፍን ብሩ፡አሊ ሚራ፡ስሜነህ ደስታ በሀገረማርያምና በሻሸመኔ አካባቢ በሸፈቱት፡በሸንኮራና በምንጃር አካባቢም ሸፍተው ባሉትና በገጠሩ በመጠናከር ላይ ባሉት የባላባቱ መደብ ርዝራዦች ላይ አንዳችም እርምጃ አልወሰደም፡፡እነዚህንና ወደውጭ የወጡትን አድሃሪዎች ጸረሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ በሚያስተባብረውና በደርጉም በራሱ ውስጥ ስርጎ በገባው ባሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ላይ አንዳችም እርምጃ አልተወሰደም፡፡ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሀያ አመት ሙሉ ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ በላይ አውጥቶና ወደስድሳ አምስት ሺህ የሚጠጉ የያንኪ ወታደሮች አሰልጥኖ በታላቅ ውርደት ከኢንዶቻይና በህዝብ ትግል ተባርሮ ሲወጣ፡የኢንዶቻይና ህዝቦች ድል የአለም ጭቁን ህዝቦች ሁሉ — የኢትዮጵያ ህዝብም ጭምር — ድል መሆኑ እየታወቀ፡ወታደራዊው መንግስት ገና መንግስታቸውን አላወቀም፡፡የኢትዮጵያ ህዝብም የዚህን ድል ትልቅነትና ምሳሌነት እንዳያውቀው ተደርጓል፡፡ይህ ሁሉ ወታደራዊው መንግስት በአድሃሪ ሃይሎች ቁጥጥር ስር እየወደቀ በመሄድ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡

6ኛ/ ወታደራዊው መንግስት በያዘው አድሃሪ ጐዳናበመግፋት አሁን በመጨረሻ የኢትዮጵያን ሰራተኞች አንድነት ማህበር ዋና መስሪያቤት ዘግቷል፡፡የመንግስቱ መግለጫ እንደሚለው ሁሉ በርግጥ ይህ ድርጅት መጀመሪያ ሲቋቋም ለፊውዳሉ ስርአትና ለኢምፔሪያሊዝም አገልግሎት ነበር፡፡ነገር ግን ለፊውዳሉ ስርአትና ለኢምፔሪያሊዝም አገልግሎት ያልተቋቋመ የመንግስት ድርጅት የትኛው ነው፡፡እንዲያውስ የኢትዮጵያ አብዮት አንዱ ዋና ጠላት ጠቅላላው ቢሮክራሲ አይደለምይ?

በኢሰአማ ውስጥ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የቆየው ትግል በነአለም አበባ አድሃሪ ክንፍና በተራማጁ ክንፍ መካከል የነበረው ነው፡፡ተራማጁ ክንፍ የጠየቀው ይህ ትግል በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲፈታ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ ነው፡፡ወታደራዊው መንግስት ግን የዚህን ክንፍ ትክክለኛ ጥያቄ ችላ በማለት እነአለም አበባን ከስልጣን ላይ ካቆየ በኋላ አሁን ሁለቱንም

ወገኖች ያለአገባብ በአንድ አይነት በማየት መሰሪያ ቤቱን እስከመዝጋት ደረሰ፡፡ በዲሞክራሲያ
ዊ መፍትሄ ፈንታ የጉልበትን መፍትሄ መርጧል ማለት ነው፡፡ ይህም የሚወገዝ እርምጃ ነው፡፡
በኢሰአማ ውስጥ ያለው ቅራኔ በውስጡ ባሉት ሃይሎች ትግልና በዲሞክራሲ እንጂ በጉልበት
የሚፈታ አልነበረም፡፡ አይደለም፡፡

7ኛ/ ከስድስት ሳምንት በፊት የመንግስት ገልበጣ ሙከራ ተደርጎ እንደነበረ ማንም የሚ
ያውቀው ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ወታደራዊው መንግስት ስለዚህ ጉዳይ አንዳችም መግለጫ ለሕ
ዝብ አላቀረበም፡፡ የመንግስት ገልበጣው ሙከራ የተደረገው በደርጉውስጥባሉ አድሃሪ ሃይሎች
መሆኑ እየታወቀ፡ መንግስቱ መግለጫና ማብራሪያ ለማውጣት አለመመከሩ በደርጉ ውስጥ የአድሃሪ
ያችን መጠንከር ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ሌሎችንም ብዙ ምሳሌዎች ለመጠመር ይቻላል፡፡
የኤርትራ ጥያቄ፡ የቢሮክራሲው ጠቅላላ ባበታጁ፡ የምስጢር ፖሊሱና የባንኩሩ ሁኔታ ሁሉ በዝር
ዝር መጠቀስ በተገባቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ወታደራዊው መንግስት ባድሃሪ ሃይሎች
ስር ለመውደቁና አ-ሃሪያች እየተጠናከሩ፡ የደርጉም ቀራማጁ ክንፍ እየተዳከመ፡ ለብቻው እየተ
ነጠለ ለመሄዱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ
የመቀልበስን ጉዳና ይዞአል፡፡ ይሁንናም ይህ መቀልበስ ቢደረግም፡ ተራማጆች ሁሉ ቢታሰሩና ቢገ
ደሉም፡ ያሜሪካን ኢምፔሪያ-ሊዝምና አድሃሪያች የቀ-ነን ድል ቢያገኙም ሰፊው የኢት-ጵያ ሕዝ
ብ የመጨረሻውን ድል የቀዳጃል፡፡

ስለዚህም የወዘአደሩ ተራማጆች፡ የኢትዮጵያ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፡ በልዩ ልዩ የመንግስት
መ/ቤቶች /ለምሳሌ በንግድ ሚኒስቴር፡ በፍርድ ሚኒስቴር፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ፡ በመሬት
ይዞታ ሚኒስቴር.../ የሚገኙ ተራማጅ ሰራተኛ፡ ተማሪዎችና የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች፡ ባጭሩ
ጠቅላላው ተራማጅ ምሁራን ደጋግመው እንደጠየቁት ዲሞክራሲ መብቶች ባይውሉ ባያድሩ ከስራ
ላይ መዋል አለባቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ተራማጆችና በጠቅላላው የሰፊው ህዝብ ወገኖች በዚህ
በዲሞክራሲ ግንባር የሚያካሂዱትን ትግል ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እንደሚገፉበት ጥርጥር
የለንም፡፡ የጊዜው ዋና ጥያቄ ይህ የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ነው፡፡

የታሰሩት ተማሪዎችና ተራማጆች በሙሉ ይፈቱ

ዲሞክራሲ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ

አድሃሪዎችና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል